# የባንክ ሒሳብ ቁጥራቸውን አስገብተው መረጃቸውን ማግኘት ላልቻሉ ጥቂት አመልካቾች የተዘጋጀ አጋዥ ጽሑፍ

በ http://aahdab.et/saving ድረ-ገጽ ላይ የባንክ ሒሳብ ቁጥርዎን አስገብተው መረጃዎን ማግኘት ካልቻሉ፤ '**መረጃ ያላገኛችሁ በዚህ ሊንክ ተጠቀሙ**' የሚለውን መስፈንጠሪያ በመጫን ወይም በቀጥታ ወደ http://aahdabsaving.gov.et/ በመሄድ ያመልክቱ።




## በቅድሚያ:- ወደ መነሻ ገጽ መግባት

- http://aahdabsaving.gov.et/ ድረ-ገጽን ይክፈቱ። በመነሻ ገጹ ላይ የሚከተሉትን ሁለት አማራጮች ያገኛሉ:-
  - "**በምዝገባ መለያ ቁጥር ያመልክቱ**":- ይህንን አማራጭ በመጫን የቀረቡትን ቅጾች ሞልተው እና የሚጠየቁትን ሰነዶች (የምዝገባ ማረጋገጫ ወረቀት እና የባንክ ደብተር የሒሳብ ቁጥሩ የሚገኝበትን ገጽ) አያይዘው ፎርሙን ይሙሉ ።
  - "**የማመልከቻ ሁኔታዎን ይከታተሉ**":- ቀደም ብለው ፎርሙን ካስገቡ በኋላ፣ ሂደቱ የደረሰበትን ደረጃ ለመከታተል ይህንን አማራጭ ይጠቀሙ።



## 1. በምዝገባ መለያ ቁጥር እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

- የምዝገባ መለያ ቁጥርዎን (ID) ለማስገባት በመጀመሪያ "በምዝገባ ቁጥር ያመልክቱ" የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።




### በቅድሚያ፦ የምዝገባ መለያ ቁጥር (ID) ያስገቡ

- የ15 አሃዝ የምዝገባ መለያ ቁጥርዎን ያለ ምንም ክፍተት እና በትላልቅ (Capital) ፊደላት ብቻ ይጻፉ፤ ለምሳሌ፦ AD01G******2005። ቁጥሩን በትክክል ማስገባትዎን ካረጋገጡ በኋላ "መረጃ አረጋግጥ" የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ። መረጃው ስህተት መሆኑን የሚገልጽ መልእክት ካሳየዎት አጻጻፍዎን በድጋሚ ይፈትሹ።



## ቀጥሎ፡- የግል መረጃዎን ይሙሉ



- እባክዎ የሚከተሉትን መረጃዎች በትክክል ይሙሉ፡- ሙሉ ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር፣ ጾታ፣ የቤት ልማት ፕሮግራም፣ የመኝታ ክፍል ብዛት እና ስልክ ቁጥር።
    - ማሳሰቢያ፡- ሁሉም መረጃዎች የግድ አስፈላጊ (Mandatory) ስለሆኑ ባዶ ቦታ መተው አይቻልም።

## በመቀጠል፡- ሰነዶችዎን ያያይዙ



- እባክዎ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ያለበት ገፅ እና የምዝገባ ሰነድዎን ያያይዙ።
    - የሰነድ ቅርጸት (ፎርማት) ፡- JPG፣ PNG ወይም PDF መሆን ይኖርባቸዋል።
    - የመጠን ገደብ፡- እያንዳንዱ ሰነድ ከ 20mb መብለጥ የለበትም።
- ሰነዶቹን መርጠው ከጨረሱ በኋላ '**መረጃ አስገባ**' የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።

## በመጨረሻ፡- መረጃው በተሳካ ሁኔታ መግባቱ ተረጋግጧል




- የመረጃ ማስገባት ሂደቱ በተሳካ ሁኔታ ስላጠናቀቁ አሁን ይህንን ገጽ መዝጋት ይችላሉ።
    - **ክትትል**፡- የማመልከቻዎን የሂደት ሁኔታ በዚህ ገጽ ላይ ወይም በዋናው ገጽ ላይ የሚገኘውን «**የማመልከቻ ሁኔታዎን ይከታተሉ**» የሚለውን መከታተያ በመጠቀም መከታተል ይችላሉ።

## 2. የማመልከቻ ሁኔታዎን እንዴት መከታተል ይችላሉ?

### በቅድሚያ:- ያመለከቱትን መረጃ:



- "እባክዎ ባለ 15 አሃዝ መለያ ቁጥርዎን (ID) ያስገቡና 'ፈልግ' የሚለውን ይጫኑ።
  - ስህተት ካጋጠመዎት: የጻፉትን መረጃ ትክክለኛነት ያረጋግጡ። (ከ7 ሙከራዎች በኋላ በድጋሚ ለመሞከር ለ2 ደቂቃ በትዕግስት መጠበቅ ይኖርብዎታል)።

### በመጨረሻ:- ሁኔታዎን ይመልከቱ



- **በመጠባበቅ ላይ**
  - ቢሮው ያቀረቡትን ዲጂታል መረጃ ተረክቧል። ከዋናው የመረጃ ቋት ጋር ሙሉ በሙሉ መጣጣሙን ለማረጋገጥ በሚመለከተው ክፍል ምርመራ እየተደረገለት ይገኛል።



- **ተቀባይነት አግኝተዋል**
  - የማረጋገጫ ሂደቱ ተጠናቅቋል። ያስገቡት መረጃ ትክክለኛነት ተረጋግጦ፣ ወቅታዊ ሁኔታዎን እንዲያንጸባርቅ መዝገብዎ በቢሮው ዋና የመረጃ ቋት ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ተረጋግጧል።



- **ውድቅ ተደርጓል**
  - ያቀረቡት ማስረጃ ከይፋዊ መዝገቦች ጋር ሊጣጣም አልቻለም። የመዝገቡን ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል በዲጂታል መንገድ ተጨማሪ ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም።